## <u>የረቡዕ ሚያዝያ 24 1997 ዓም ( ሜይ 3 2005 )</u>

## <u>የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ</u>

## <u>ጅብ የሚያነክሰው ሜዳ እስኪደርስ ነው</u>

*እኛማ ተናግረን ነበር የሚሰማን አጣን እንጅ ÷ ለማለት ባንፈልግም÷ የወያኔ መሪዎችን ባኅርይ÷ ስብዕናም ይሁን ተግባር እየተከታተልን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስንናገር መቆየታችን ለማንም ግልፅ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ያስቻለንም ከተፈጠሩ ጀምሮ በሚገባ ስለምናውቃቸውና ስለምናውቅባቸው ነው፡፡ ለዚህም ይመስለናል÷ የወያኔ መሪዎች ከማንም በበለጠ ኢሕአፓን የሚጠሉትና የሚፈሩት፡፡ የሕዝባዊው አመለካከትና አባባልም በበኩሉ የወያኔን መሪዎች ማንነት የሚገልፅ እንጉርጉሮ ማሰማቱን አላቋረጠም፡፡ "ተናግሬ ነበር በአጥር ተንጠልጥየ÷ ወያኔን ከሰማህ ትጠፋለህ ብየ" እየተባለ በየቦታው የሚነገረው÷ ከጭፍን ጥላቻ ሳይሆን÷ ወያኔዎቹን በትክክል ለመግለፅ የሚደረግ ሙከራ ነው፡፡ የወያኔ መሪዎች የሚናገሩትና የሚሰሩት ተገጣጥሞ ስለማያውቅ÷ በአሁኑ ወቅት÷ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚገባውን ያህል ማንነታቸውን በትክክል ሊረዳ ከሚችልበት ደረጃ መድረሱ የሚካድ አይደለም፡፡ መለስና ግብረ-አበሮቹ ለተግባራቸውና ለሰብዕናቸው መሸፈኛ የተላበሱት መርኅ÷ <u>መስሎ መታየትና ሆኖ መገኘት</u> በሚል ስነልቦና ማጠንጠኛ የሚሽከረከር ነው፡፡ ውሸትንና ቅጥፈትን እንደ መንግሥታዊ መመሪያ አንግቦ የሚራመድ አስተዳደር በኢትዮጵያ ምድር በዚህ አሳፋሪ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተው በዘመነ ወያኔ መሆኑ÷ በአሁኑ ስዓት ሀገር ያወቀው ፀሀይ የሞቀው ሀቅ ሆኗል፡፡ ይህን ሀቅ የተረዳው ሕዝብም ከእንግዲህ ወዲህ ምን መደረግ አለበት? የሚለውን አቅጣጫ ለመያዝ በመነጋገር ላይ ነው፡፡ ይህ መደገፍ ያለበት ሕዝባዊ ሂደት ይመስለናል፡፡ የወደፊት ዕድልን በሚወስን ርምጃ ላይ መረባረብ እንጅ÷ በአለፈ ሰቆቃና ችግር ላይ ቢያነበንቡ ፈውስ አይሆንምና ነው፡፡*

*የሚገዙትን ሕዝብ በፕሮፓጋንዳ ነጋሪት ማደንቆር የአምባገነኖች ዓይነተኛ የአገዛዝ ስልታቸው መሆኑ አይዘነጋም፡፡ ይልቁንም ይህ ስልት በተጠናከረ መልኩ በተግባር የሚተረጎመው÷ ህዳጣን በሆኑ ወይም ሰፊ ድጋፍ በሌላቸው መሪዎች ነው፡፡ የእንደነኝህ ዓይነት መሪ ጭንቀትና ፍርኃት ልክ በጠላት ጦር እንደተከበበ ሠራዊት መርበትበትና መጨነቅ ነው፡፡ ዙሪያው ሁሉ ጠላት ይመስለዋል፡፡ ጥላውን እያየ ይበረግጋል፡፡ ነፋስ በነፈሰ ቁጥር ይርበተበታል፡፡ መውጫ ቀዳዳ ፍለጋ ለማግኘት ይጠራወታል፡፡ በአጥፍቶ መጥፋት አዙሪት ይወዘወዛል፤ይወራጫል፡፡ ከእዚህ ሁሉ ፍዳና መከራ ለመውጣት የማይፈነቅለው ድንጋይ አይኖረውም፡፡ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሰሞኑን እየወሰደ ባለው እርምጃ ከላይ የተገለፀውን ባኅርዩን አስመስክሯል፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ ይካሄዳል በሚለው የግንቦቱ ምርጫ የተቃዋሚ ድርጅቶችን የተጠናከረ ከበባ በመፍራት÷ ከአሁኑ ብዙ ሰዎችን እያሰረ÷ እያሳደደ÷ እየገደለ÷ ሀብት እየዘረፈና እያስፈራራ ይገኛል፡፡ ከአሁኑ÷ የምርጫ*

ካርድ እየቀማ መስብሰብ ጀምሯል። የምርጫው ቀን ሲመጣ ወደ ራሱ የምርጫ ሳጥን ለመክተት! ይህ የግንቦት ምርጫ ለወያኔ መሪዎች፥ የሞትና የሽረት ጉዳይ ሆኖባቸዋል። ምርጫው ፍትኃዊና ነፃ ሆኖ ሕዝቡ የሚፈልገውን በመምረጥ ወያኔ ይሸነፋል የሚል ብዥታ እንኳ አለ ባይባልም፥ እናም ደግሞ፥ ያው እንደተለመደው ወያኔ ማሸነፉ የታወቀ ቢሆንም፥ የወያኔ መሠረት ያው ህዳጣን ስለሆነ፥ መለስና ተባባሪዎቹ ምን ጊዜም ቢሆን በሙሉ ልብነት ሊተማመኑ አይችሉም። እረ ኋላ ጉድ እንዳንሆን? የሚል ጠንካራ ስጋት አላቸው። ይህ ስጋታቸውና ፍርኃታቸው ታዲያ በግድ፥ እንደቆሰለ አውሬ መጨነቅና መጠበብን አስከትሎባቸዋል። በግድ ምርጫውን ማሸነፍ አለበን፥ ያለዚያ የሚሆነው አይታወቅም ከሚል የወንጀለኞች ስሌት፥ የመጨረሻ ስዓት ውንብድናቸውን ቀጥለዋል።

ውንብድናው ደግሞ አንድ ፥መንግሥት ነኝ ከሚል ቡድን እንደሚፈፀመው ድርጊት ሳይሆን፥ ልክ አንድ ማፍያ ወይም የቀማኛ ድርጅት እንደሚያከናውነው ወንጀል ነው። ሰሞኑን በመቀሌ ከተማ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት በጠራው ስብሰባ የወያኔ ታጣቂዎች የፈፀሙት ድርጊት፥ ልክ አንድ ወንበዴ ድርጅት እንደሚፈፅመው ዓይነት ነበር። እነኝህ ታጣቂዎች ወደ ስብሰባው አዳራሽ በኃይል በርግደው በመግባት፥ የጠረጠሯቸውን ሰዎች ለይቶ በመደብደብ፥ ሌሎችንም አፍነው ወደ አልታወቀ ቦታ ወስደዋቸዋል። የመድረኩን ተናጋሪዎች ለማፈን ሞክረውም በአዳራሹ የነበረው ተሰበሳቢ ሆ! ብሎ በመነሳት ድርጊቱን እንዳይፈፅሙ ከልክሏቸዋል። ይህ ሁሉ ድርጊት የሚፈፀመው፥ መንግሥት ነኝ በሚል ቡድን ትዕዛዝም መመሪያም ነው። መጭውን መርጫ አስመልክቶ፥ የወያኔ መሪዎች የሚያደርጉት ወንጀል እንዳይታወቅባቸው፥ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ታዛቢዎችን እንዲታገዱ አድርገዋል። በርካታ የውጭ ታዛቢዎች ከሀገሪቱ ተባርረዋል። ሀገር በቀል ታዛቢዎችም በየምርጫ ጣቢያዎች ዝር እንዳይሉ ተደርገዋል። በድርጊቱም የውጭ ደጋፊዎቻቸው እንዳልተደሰቱ ይነገራል። በግልፅ ተቃውሞ ሲያሰሙ ግን አልተደመጠም። ይህንን ለማድረግ ያለወሰኑበት ምክንያት አላቸው ብለው የሚያስቡ የፖሊቲካ ታዛቢዎች አልታጡም። እንደታዛቢዎቹ አባባል ከሆነ፥ እነዚህ ምዕራባውያን የበላይ ጠባቂዎች፥ ወያኔን ለመለወጥ የሚያስችላቸውን አስተማማኝ አዲስ ሎሌ ለማዘጋጀት በመጣደፍ ላይ ስለሆኑ፥ ያ እስኪሳካላቸው ድረስ፥ ወያኔን በግልፅ ከመቃወም ተቆጥበዋል የሚል ነው። አስተማማኝ አዲስ አገልጋይ ማግኘታቸውን ከአረጋገጡ ግን በፈለጉት ወቅት ወያኔን ለመለወጥ ወደኋላ እንደማይሉ የሚያጠራጥር አይሆንም። ወያኔም ይህንን ጉዳይ ይዘነጋዋል አይባልም። ለዚህም ነው በግንቦቱ ምርጫ በሆነው መንገድ አሸናፊ ነኝ ብሎ ለማወጅ የሚጥረው። ይህን ለማሳካትም ነው፥ሰው ማሰር መደብደብ፥ ማሸበር፥ መግደልና ሀብት መዝረፍን የተያያዘው። ሕዝቡን ለማስፈራራትና ለማሸበር ሲልም፥ የሴት ልጅ ጆሮ እስከ መቆረጥ ደርሷል። መቸም የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ነገር መስማማት ሊኖርበት ነው። የግንቦቱ ምርጫ በወያኔ ማጭበርብር ምክንያት ሕዝባዊ ውጤት ስለማያስመዘግብ፥ ከግንቦት በኋላ የሚደረገው ሕዝባዊ ትግል በአዲስ ዘዴና ስልት ተቀይሶ መመራት

መታገል እንዳለበት ነው፡፡ የወያኔ ምርጫ የወያኔ እንጅ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ገንዘብ ስለአይደለ፥ ሁሉም ማተኮር የሚገባው የቀጣዩ ትግል ምን መሆን እንዳለበት ሀገራዊ ጥሪና ክተት መደረግ አማራጭ የሌለው ይሆናል፡፡ በቶጎ ሀገር ሕዝቡ የተጭብርብር ምርጫን በመቃወም እያካሄደ ያለው አመፅ ምሳሌ ነው፡፡ ሆስፒታል ከመድረሱ በፊት ስለሞተው የወያኔ ምርጫ ማውራትና መበሳጨቱ ፍሬ ቢስ በመሆኑ፥ ሀገራችንን ከወያኔ መዳፍ ለማላቀቅ በሚያስችለው የወደፊቱ ዘላቂ ና ፍቱን ትግል ላይ መረባረብ ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ አይሆንም፡፥ ማን ምን ያህል መቀመጫ አገኘ?፥ በአዲሱ የነወያኔ ካቢኔ ማን ሚኒስቴር ሆነ? ማን ተሾመ--ተሻረ? ወዘተ እያሉ በፈረሰው የወያኔ የተስካር ዳስ ውስጥ ገብቶ ከመዳከር፥በራስ አጀንዳና ራዕይ፥ በራስ የትግል መድረክና ኃይል እያተኮሩ መታገል ሀገርን ነፃ ለማውጣት አስተማማኝ ውጤት ያስገኛል፡፡

ከግንቦቱ የወያኔ ምርጫ በኋላ፥ መለስና ኩባንያው "ፍትሃዊና ነፃ" ምርጫ አካሄደን አሸንፈናል ብለው ያውጃሉ፡፡ የዘረኛ ሥርዓታቸውንና መዋቅራቸውን ሳይለውጡም አዲስ አስተዳደር አቋቁመናል በማለት እራሳቸውን ደልለው፥ ሌላውን ለማታለል ይጥራሉ፡፡ የአምባገነን ኃይላቸውን አጠናክረው ለመግዛት ወደኋላ አይሉም፡፡ የሀገሪቱ ሁለንተናዊ ሁኔታም በከፋ መልኩ እየተባባሰ ይቀጥላል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብም አልገዛም ባይነቱን አጠናክሮና አስፋፍቶ መታገሉ የታሪክ ሀቅ መሆኑን ያስመሰክራል በለን ተስፋ አለን፡፡ በወያኔና በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል፥ማለትም በአምባገነን ሥርዓትና ሥርዓቱን ተቃውሞ በሚታገለው ሕዝብ መካከል ቅራኔው እየሰፋ፥ እየከፋ፥ እየከረፋ፥ እየጋለ፥ አርድ አንቀጥቅጥ ደረጃ ይደርሳል፡፡ ወያኔም በበኩሉ ፥ ሕዝባዊ ትግሉን፥ ለማስተንፈስ፥ ለማልፈስፈስ፥ ለማጨናገፍ፥ ለማኮላሸት፥ ለማዳፈን፥ ለመከፋፈል፥ ከቻለም ጨርሶ ለመግደል ወይም በተመለምዶ እንደሚለው፥ ለማምከን የማይፈነቅለው ድንጊያ አይኖርም፡፡ ይህ ካልተሳካለት ደግሞ ኃይል መጠቀሙ የሚካድ አይሆንም፡፡ ይህን አስመልክቶ፥ ማነኛዎቹም አምባገነኖች ተመሳሳይ ርምጃ በመውሰድ ረገድ አንድ አካል አንድ አምሳል ናቸው፡፡ ሂትለር፥ ቡናማ ሸሚዝ ለባሽ (ብራውን ሸርት) ወይም ( ስቶርም ትሩፐስ)፤ ሙሶሊኒም፥ ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ( ካሚቻ ኔራ)፥ በሀገራችንም ቢሆን፥ በአፄው ዘመን፥ ፈጥኖ ደራሽ፥ በዘመነ ደርግ፥ ነበልባል ጦር፥ ወያኔዎቹም፥ ፌዴራል ፖሊስ በሚል ፀረ ሕዝብ የሆኑ ነፍሰ-ገዳይ ታጣቂ ኃይሎችን በማሰማራት ሕዝብን ይጨፈጭፋሉ፡፡ የወያኔው ፌዴራል ፖሊስ ከሌሎቹ የሚለየው ባኀርይና ድርጊት፥ " ግደልና ጠይቅ" የሚል ቋሚ መመሪያ ያለው መሆኑና ፥ እንኳንስ ሠላማዊው ዜጋ ቀርቶ፥ የመደበኛው ፖሊስ ሠራዊት ሳይቀር፥ የሚፈራው መሆኑ ነው፡፡ ይህ ፋሽስታዊ የሆነው የፌዴራል ፖሊስ፥ ለጭፍጨፋ በሚሰማራበት ጊዜ፥ ከፍርኃቱ የተነሳ፥ መደበኛው ፖሊስ ከሠላማዊው ሕዝብ ጋር አብሮ ሲሸሽ ማየት፥ ዛሬ ያልተለመደ አይደለም፡፡ ይህ የሚያመለክተው፥ እነኝህ የወያኔ ፌዴራል ፖሊስ አባሎች፥ የቱን ያህል ጨካኞችና አስፈሪዎች መሆናቸውን ነው፡፡

በዘመናት፥ አምባገነኖች የጭካኔ አገዛዛቸውን ለማራመድ፥ የተለያዩ ጭፍጨፊ ኃይሎችን ቢያሰማሩም፥ በመጨረሻው ግን የሕዝብ ትግል አሸናፊ መሆኑ ታውቆ፥ የተቃዋሚ ኃይሎች፥ ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ ምንም ለውጥ አለመኖሩን በመረዳት፥ ሕዝቡን አስተባብረው ትግሉን ማፋፋም አለባቸው። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ማዕከል ትላንትም ሆነ ዛሬ ፓርላማ የሚባለው የቀልድ ቦታ አይደለም። ሰለዚህም ለሀገር ቁም ነገር ያለው ሥራ ሊሰራ የሚችለውም ከዚሁ መድረክ ውጪ ነው። ወያኔ ራሱ የራሱን ፓርላማ ከቁም ነገር ሲቆጥረው አልታየም። የመለስ ቡድን የሚፈራውና እየጨነቀው ያለው ተቃዋሚ ኃይሎች ሕዝብን በማነሳሳትና በማደራጀት በኩል ተገቢውን እርምጃ እየወሰዱ በመሆናቸው ነው። ስለዚህም የነገው ምርጫ መጭበርብሩ ሰለማይቀር ከወዲሁ ይህን የቅጥፈት ውጤት አንቀበልም ብሎ ሕዝብ ተቃውሞውን እንዲያሰማ፤ እንዲያምፅ፤ እንድ ዩክሬይንና ቶጎ ሕዝብ እምቢኝ! አልገዛም! እንዲል ማደራጀትና ማታገል ያስፈልጋል። ተቃዋሚ ኃይሎች መቶ መቀመጫ አገኙ ወይ መቶ ሀምሳ የሕዝብ አመፅ ያላጀበው ትግል እምብዛም ፍሬ አይኖረውም። የትግሉ መጨረሻ ከመለስ መንጋ ጋር በወያኔ ፓርላማ መነታረክ ሳይሆን፥ አገዛዙንን መጣል ማስወገድ ነው። ከዚህ ሌላ አማራጭ መፈለግ፥ የወያኔን የዘረኛ አገዛዝ ዕድሜ ከመቀጠል በቀር የሚያመጣው ፋይዳ አይኖርም። የወያኔ መሪዎች አድፍጠው መቆየታቸው፥ ጅብ የሚያነክሰው ሜዳ እስኪያገኝ ድረስ ነው ከሚለው ይትባኃል የተለየ አይሆንምና አገዛዙ ለመጣል የሕዝብን አመፅና ትግል እናጠናክር።